# Tower in the sky(የሰማይ ላይ ግንብ)

የመፅሀፉ ርዕስ፡-Tower in the sky (የሰማይ ላይ ግንብ)

ደራሲ፡- ህይወት ተፈራ

አሳታሚ፡-አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ

የገፅ ብዛት፡-437

የታተመበት ዘመን፡-እ.አ.አ.2012

የመሸጫ ዋጋ፡-74 ብር

## በሰለሞን ኃይለማርያም

ይህንን መፅሀፍሳነብበልጅነቴበአንድ ዕለተ ሰንበት አናቴእጂን ይዛ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትወስደኝ የተመለከትኩትን ልክ እንደፊልም ወደሁዋላ ወስዶእንዳስታውስአደረገኝ። ያኔየተመለከትኩት በነጭጋቢዎች የተጠቀለሉ የወጣቶች ሬሳ በግራና በቀኝ ተደርድሮ ነበር።

የሰማይ ላይ ግንብ ሲጀምር ደራሲዋ የተማሪ ቤትእና የልጅነት ህይወቷን እንደዋዛ በመተረክ ቀስበቀስ ከሀረር ወደ አ.አ. አመጣጥዋን፤በጊዜው የነበረውን የወጣትነትህይወት የወቅቱን የወጣቶች የልብ ትርታ ይዘረዝራል።

የአዲስ ተማሪዎችን የዩኒቨርስቲ ቆይታ፡የነበራቸውን ስሜት እየዳሰሰና እያዋዛ ወደ ዋናው የመፅሀፉ ይዘት ይዞን እልም ይላል።

በተለይበመጀመሪያዎቹ መቶ የሚሆኑገፆች አንዳንድ ታሪካዊ ዳራዎችን ዘርዝር አያደረገ ለወጣቶችና ለውጭ ሀገር አንባቢዎች እንዲገባ ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

የዘውዳዊውስርአት ሲገረሰስና አብዮቱ ሲቀጣጠል ገና ለጋ በመሆኔ የዛን ጊዜ የነበረው ትውልድ ከኔ ጋርለጥቂትበመተላለፋችን የተነሳ ስለዛ ትውልድ በተነሳ ቁጥር የማወቅ ጉጉቴከፍተኛ ነው። በዚህም ምክንያትስለትውልዱ የተጻፉመፅሀፎችን በተቻለ መጠን ሳነብቆይቻለሁ። ይሁንና የሰማይ ላይ ግንብን በመሰለ ሁኔታ በዝርዝር፤በጥልቀት፤ ሳቢ በሆነ መልክና በግልፅ መንገድ የቀረበ መፅሀፍ አላጋጠመኝም። ይህንን መፅሀፍማንበብ የጀመረ ሰው እስከመጨረሻው እንዲገፋ የሚያደርግ ጥበብ ተጨምሮበታል።

መፅሀፉበወቅቱ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች አባላትን እንዴት እንደሚመለምሉ፤የተማሪዎች እንቅስቃሴም እንዴት እያደገ፤እየተወሳሰበና የሀገሪቱ አብይ ጉዳይ ለመሆን እንደቻለ በስድ ንባብሳይሆን ልብ ወለድ በመሰለ ልብን በሚያንጠለጥል መልክ በተከሸነ አፃፃፍ የተቀመረ ነው።

እያንዳንዱ ምዕራፍ ወይም አብይ ጉዳይ ከመጀመሩ በፊት ከምዕራፉ ወይም ጉዳዩ ጋር የተገናኙ ምርጥ ጥቅሶች ከነደራሲያቸውበመገኘታቸውለመፅሀፉቅመም ሆኖታል።

መፅሀፉ የአንዲት ወጣት ኢትዮጵያዊት የህይወት ታሪክ እንዴት ከሀገራችን የፖለቲካህይወት ጋር እንደተሳሰረና እንደተጣመረ የሚያሳይ ነው። በተጨማሪም የኢትዮጵያ የፖለቲከ ታሪክ ዘውዳዊውስርአትከወደቀጀምሮ እስከ ደርግ ስርአት መንገዳገጃ ድረስ ያለውን

የወጣቱን የፖለቲካ ተሳትፎ፤የአንድ ትውልድ ተጋድሎንና ህይወትቁልጭ አድርጎ አጅግ በተጠበበ መንገድ የሚገልፅ ሆኖ አግኝቼዋለሁ::

በዚህ የህይወት ታሪክ መፅሀፍ (የኢትዮጵያ የወጣቶች የፖለቲካታሪክ መባልም ይችላል) አንደኛው ዋና ተዋናይ ጌተቸው ማሩ የተባለ ወጣት ሲሆን የጌታቸውና የደራሲዋ ጥምረት ለደራሲዋ የአስተሳሰብና የህይወት ልዕልናና ልቀትመሰረት ሲሆን ይታያል::

ጨዋታ ወዳድ፤ፍልቅልቅና እንደአበባ የፈነዳችውደራሲ ከሳቅና ጨዋታያለፈ ልዩ አለም ውስጥበመግባትበመጀመሪያ«ለአብዮት»በመቀጠልም በኢ.ህ.አ.ፓ. ውስጥቁልፍ ሚና ከነበራቸው ተዋናዮች መከከል አንድዋ ሆና ለመገኘት ችላለች::

በመፅሀፉ ምዕራፎች መግቢያ ላይ ያሉት ምርጥ ምርጥጥቅሶች ብቻ ሳይሆኑ በየመሀሉ የሚመዘዙሀሳቦች አንዲሁም በየአጋጣሚው የተዘረዘሩ ብዙ የመፅሀፍ አርዕስቶች የደራሲዋን ጉምቱ አንባቢነት፤ጥልቅ ተመራማሪነት አንፀባርቀዋል::አንባቢያንም ደራሲዋ ያነበበችውን መፅሀፍት አንዲያነቡ የሚያበረታታ ነው::

በመፅሀፉ የተዘረዘሩ የጓደኞቿስሞች፤በወቅቱ የነበሩ የፖለቲካ ተዋናዮችን አንዲሁም ዝርዝር ጎዳዮች በጥንቃቄበመዘርዘራቸው የደራሲዋን ድንቅ የማስተወስ ችሎታ ማሳየት ብቻ ሳይሆን የበለጠ ለመመራመር ለሚፈልጉ፤መፅሀፉን ወደፊልም ሲቀይሩት ለሚመኙ ምቹ ሁኔተዎችን የፈጠረ ነው::

**Tower in the sky** (የሰማይ ላይ ግንብ) አንደተወርዋሪ ኮከብፉ ብሎ የታየውን የዘመኑን ወጣቶች ስሜት፤አስተሳሰብ፤ስነልቦና፤አስተዳደግ፤ምኞት፤ትጋት፤ቁርጠኝነትና አርቆ አስተዋይነት በዝርዝር፤በማስረጃ አንዳይሰለች ሆኖ እያዋዛ የቀረበ ወደፊትም የኢትዮጵያ የፖለቲካታሪክ በተነሳ ቁጥር ተደጋግሞ መዘከሩ የማይቀር መፅሀፍእንደሆነ ተሰምቶኛል::

«ታሪክ ያለፉትን ተከታታይ ትውልዶች ከዛሬውና ከወደፊት ትውልዶች ጋር የሚያገናኝ የሚያስተዋውቅና የሚያስተሳስር ሰንሰለት ነው::»(መክሸፍእንደ ኢትዮጵያታሪክ፤መስፍን ወልደማርያም፤2005 ኢ.ም.ገጽ 35) ይህም መፅሀፍአንደሻማቀልጦ፤ህይወቱን ገብሮ ለዚህ ትውልድ ታሪክ ሰርቶ ያስተላለፈውን ትውልድ ተጋድሎ ከአሁኑ ትውልድ ጋር ለማስተሳሰር የሚረዳ አንድ ጠንከራ የሰንሰለቱ አካል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል::

በመፅሀፉደራሲዋ ከህሊናዋ ጋር ያደረገችውን፤ የታገለችውን በመጨረሻም ነጥሮ የወጣውን የአስተሳሰቧን፤ የዘመን ሽግግር አድገትና ንረት ታሳየናለች:: የደራሲዋ የመጀመሪያ ክርስትናዋ ማርክሲዝም ሲሆን ለድርጅቷ ህይወቷን ብቻ ሳይሆን ነፍሷን ጭምር ሰጥታቆይታለች:: ነፍሷን የሰጠችውም ወዳ፤ፈቅዳና ከልቧ አምናበት ነበር:: በወቅቱ ደሟ ቢመረመር ማርክሲዝም ጠብጠብሳይል የሚቀር አይመስልም:: ይህ የደራሲዋ እምነትና ተስፋ የጊዜውመንፈስ ነበር ለማለት ይቻላል:: በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ በጊዜው የነበሩ ወጣቶች ስሜትይነስም ይብዛም የደራሲዋን ይመስል ነበር ብሎ ድምዳሜ ላይ መድረስም የሚቻል ይመስላል::

«በድንገትትምህርቴን መቀጠል ራስ ወዳድነትመስሎ ተሰማኝ:: ከድህነት አረንቋ ውስጥ መውጣት ያለበትን የህዝባችንን ስቃይእያየሁ መማር ዋጋ አልባሆነብኝ:: ህዝቡእየፈለገኝ ትምህርቴን ማሳደድ ምን ይባላል? በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝባችን አንዱን እንኳሳያገኝ እንዴት ሁሉን ለማግኘት እመኛለሁ?.......ትግሉያለፈው፤ያሁኑና የወደፊቱ ህይወቴ ነው::! ገፅ 155

*«....ማርክሲዝም በዙሪያዬ ያለውን ኢ-ፍትሀዊነት ገልጦ አሳየኝ:: በዝባዥና ጨቋኝ ስርአትን እንድታገልናእንድደመስስ አመላከተኝ:: በጨቋኝ ስርአት አመድ ላይ የተሻለህይወትለመገንባት ተነሳሳሁ:: ጭንቀ፣ና ጥበትስለራሴ ደህንነትሳይሆን የህዝቡን ነፃነትለማረጋገጥ በሚደረገውትግል ራሴን መስዋዕት ለማድረግ ነበር:: ማርክሲዝም በውስጤ ያለውን መልካምነት አጉልቶ አውጥቶታል::ተስፋምሰጥቶኛል::ወዛደራዊነት ነግሶፍቅርና ደስታ ለሀገራችን ብቻ ሳይሆን በምድር ላይ ሲሰፍን በመጨረሻ ድልን ስንጉናፀፍ ይታየኝ ነበር::የመንፈስ አባቶቻችን ማርክስ፣ኢንግልስ፣ሌኒንና ማኦ 'መንግስተ ሰማያት'በቅርባችን ብቻ ሳይሆን የማይቀር መሆኑን አረጋግጠውልኛል::...»ገፅ157*

*«... በመንገድ ላይ የማያቸውሰዎች፣በታክሲ አብረውኝ የሚጓዙ፣በምግብቤት ተመጋቢዎች የራሳቸውጭንቀት፣ስጋት፣ፍላጎትና ሀዘን ያላቸው ተራ ሰዎች መሆናቸው ቀርቶ ወዝአደሮች፣አርሶአደሮች፣ፊውዳሎች፣ንዑስ ከበርቴ፣ቤሮክራቶችና ሠራተኞች ሆነው አገኘ|ቸው::....*

*«ደህና ሀብታም ማየት አቁሜ ድህነትን፣ጭቆናንና ብዝበዛን ማየት ጀመርኩ::ለለማኞችና ለአከል ጉዳተኞች ማዘን አቆምኩ::እንደድሮውምፅዋትመስጠትትቼበምትኩ ደህና ለማኝ አድርጎ ክብራቸውን የገፈፈውሥርአት ላይ ንዴተ ባሰ::...»ገፅ158*

*ጌታቸውበአሰቃቂ ሁኔታበራሱድርጅት ከተገደለ በ|ላም አንኳ ቢሆን ደራሲዋ በድርጅቷ ላይ ያላት ዕምነት የቀጠለ ቢሆንም ውስጥ ውስጡን መሸርሸሩ አልቀረም::ጌታቸው ከመገደሉበፊትደራሲዋና ሌሎች የቅርብ ወዳጆችና ጓዶች ብርሀነመስቀል ረዳ ጭምር ጌታቸውየድርጅቱ ጭዳ ከመሆን አንዲያመልጥ ቢመክሩትና ቢጎተጉቱት ጌታቸውበቅንነትምናልባትም በየዋህነት «አንዴት ድርጅቴን አንድጠረጥር ታደርጋላችሁ::ጓዶች አንዲህ አያደርጉም»በማለት ተከላክሏል::*

*የጌታቸው ከድርጅቱ መባረር፣መታገትና በመጨረሻምበራሱድርጅት ለመገደል ያበቃው«በከተማ የትጥቅ ትግል፣ፋሺዝምና ከደርግ ጋር የተባበረ ግንባር»በሚሉት ጉዳዮች ላይ በነበረው የሀሳብ ልዩነት ነበር:: ጌታቸው የሀሳብ ልዩነትን በውይይትመፍታት ይቻላል የሚል አቋም ሲኖረው ሌሎቹ ግን የተለየ አመለካከት ነበራቸው::*

*«ልዩነታቸው'አንዴትበሚለው ነበር:: ጌታቸው ማሩ ችግሩን አስቀድሞ አይቶት ነበር:: እስከማውቀው ድረስ ከሁሉም ደርጅቱን ለመልቀቅያልፈለገው እሱ ብቻ ነበር:: ውስጣዊ ዲሞክራሲያዊ ውይይት አናድርግ፣በማዕከላዊው ኮሚቴ ላይ ተፅዕኖ በማድረግ በፓርቲው ውስጥውይይትእንዲደረግ እንዲፈቅዱ ማድረግ አለብን' ይል ነበር::» ገፅ251*

*ደራሲዋ ጌታቸውበራሱድርጅት ከተገደለበ|ላ የተለያዩ ጥያቄዎች በአእምሮዋ ሲመላለስቀይተል::*

*«....ለምን ነበር የሞተው? ህይወትለማትረፍ ሲል ይሆን? ይህ ሁሉበደልበአብዩትስም ነው የሚፈፀመው?....በአብዮቱ ስም ሰውን መግደል አግባብ ነው?....አብሮን ያለውን ከገደልን እንዴት መልካም መስራትእንችላለን? በጓዳዊነት፣በፍቅርና በእምነት ጀምረን ወዴትእየሄድን ነው?ወዴትእንደምንሄድ ረሳን ማለት ነው? የጋራ ሚሽናችን የት ሄደ?» የሚሉና ሌሎች ብዙ ውሀ የሚቋጥሩ ጥያቄዎችን አንስታለች:: ገፅ270-271*

*የጌታቸው የሀሳብ ልዩነት ወሳኝ የሚሆነውምናልባትም የሙቶ ሺህ ወጣቶች ደም መፍሰስ ወይም አለመፍሰስ የሚዳኝበት ወሳኝ ነጥብ አንደነበር በመፅሀፉ በተለያዩ ቦታዎች*

ተገልፆአል፡፡በሀሳብ ልዩነቱ በሌላበኩል ያሉት እንደዚህ መፅሀፍበጥራት ማሳየት እስከልቻሉ ድረስ ይህ መፅሀፍ የጌታቸወ<ና የትግልጓደኞቹ የሀሳብ ልዩነት ነጥብፍትሀዊ እንደነበር የሚያሳምን ነው፡፡

በርግጥ ጌታቸውበራሱድርጅት ከመገደል በ|ላ ብዙ መቶ ሺህ ምርጥ፤ ብሩህና ብልህ የሀገራችን ወጣቶች እንደዋዛ ተገድለዋል፡፡የደርግ ሰይፍም ለሀገራችን የእድገትና የለውጥ መሠረት ይሆኑ የነበሩትን ወጣቶች በለጋነታቸውበአብዩትስም፤በሀገር ስም፤በጭቁኑህዝብ ስም፤በወዛደሩናበአርሶአደሩ ስምበግፍቀጥፎአቸዋል፡፡

ብዙ ሰዎች«ሀገራችን ከሀምሳና ስልሳ አመትበፊትከደቡብ ኮሪያ እኩል ነበረች እንደውም ትበልጥ ነበር» ይላሉ፡፡ «ምነው ሀገራችን ደሃና |ላቀር ሆና ቀረች» አያሉይጠይቃሉ፡፡ይህንን መፅሀፍካነበብኩብ|ላ ከዘውድ ስርአትመገርሰስቀጥሎ ለሀገራችን |ላ ቀርነትና ድህነት አንደኛ ውና ምናልባትም ዋነኛው ምክንያት በዛን ጊዜ የተሰውትና የተቀጠፉት ለሀገራችን ተስፋ የነበሩ ምርጥ፤ ብሩህና ብልህ ወጣቶችን ማጣታችን ይመስለኛል፡፡ ለአንድ ሀገር ለመማር ዝግጁ ከሆነ፤ከተማረ፤ከፍተኛ የሞራል ዝግጁነትከነበረውና እንደደራሲዋ ለሀገራቸውና ላመኑት ደማቸውን ለማፍሰስቁርጠኛ ከሆኑ ወጣቶች የበለጠ ምን ሀብት አለ?

በብዙ ሺህ የሚቆጠር ወጣት ሲገደል፤ሲታሰርና ሲሰቃይ መላው ሀገር መናጡ፤መገደሉና ሀገር መቆርቆዙ፤ሀገር መተንፈስና ማበብ አቁሞ ለብዙአስር አመታት ወደ |ላ መመለሱን ለማወቅ ብዙጥናት ማድረግ የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡፡በዚህም ምክንያት ከዘውዳዊውስርአት መውደቅበ|ላ ሀገራችን ለምን በበዙ መንገድ ወደ|ላ ቀረች ለሚለውመልሱን ይህ መፅሀፍበቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በዝርዝር ያሳያል፡፡

ለዛ ትውልድ ማለቅ ደርግን ተጠያቂ የምናደርግ እንዳለን የታወቀ ነው፡፡ ይህ መፅሀፍበወቅቱ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ከደርግ ባልተናነሰ ተጠያቂ መሆናቸውን ገሀድ አውጥቷል፡፡

ከጌታቸው መገደል በ|ላ ኢ.ሕ.አ.ፓ.ም ሆነ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች እየተዳከሙ መጥተውደራሲዋም  በመጀመሬያበከፍተኛ 19 ቀጥሎምበከርቸሌ ታስራለች፡፡በስምንት አመትከአራት ወር የከርቸሌ የእስር ጌዜዋ ሌላህይወትን ደራሲዋበመፅሀፉ አሳይተለች፡፡መፅሀፉ በብዙ ተቀጣጣይ ትረካዎች የተሞላ በመሆኑ ልብ የሚሰቅሉ ብዙ የከርቸሌ ታሪኮችም አሉ፡፡

ደራሲዋ በህይወትቆይታ ይህንን ከሀውልት ያልተናነሰ መፅሀፍያበረከተችልን በእናቷና ዘመዶቿ ተጋድሎ ነው፡፡ እናቷና ዘመዶቿደራሲዋ በህይወትእንድትተርፍ፤ከደርግጥይት አንድታመልጥ ተነግሮ የማያልቅ መስዋእትነትከፍለዋል፡፡ይህም ኢትዩጵያውያን ወላጆች ለልጆቻቸው የቱን ያህል አንደሚተጉከማሳየቱ ባሻገር በወቅቱ ግማሹ የህብረተሰብ ክፍልበማሰር፤በመግደል፤በመወንጀልና በማመስ ላይ ሲሰማራ ሌላው ደግሞ ይህንን የስቃይ ዘመን ለማለዘብ፤የታሰረውን ለማስፈታት፤ልጁን ከሞት አፍ ለማዉጣት ሲማስን ይታያል፡፡በዚህም በሀገሪቱ ይህ ነው የሚባል የልማት ተግባር አለመኖሩን መፅሀፉያሳያል፡፡

የመፅሀፉ ደራሲ በመጨረሻ ከመጀመሪያ ሀይማኖቷ ከማርክሲዝም ማፈግፈጓ አልቀረም፡፡

«'የአርትና ሙዚቃ ተሪክ' የሚለውን መፅሀፍካነበብኩብ|ላ በዕውቀታቸውና በተስጦአቸውዓለምን የሚቀይሩት ግለሰቦች ናቸው የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ፡፡ምንም እንኳመሬትን የሚያንቀጠቅጥግኝትባይሆንምለኔ በጊዜው ዓለምን በተለየ አዲስ አይን እንዳይ ረድቶኛል፡፡ ግለሰቦች ማህበረሰቡን አንደሚቀይሩ አሁን ተረድቻለሁ፡፡ በልቤ ተቀብሮ

*የነበረውን አስተሳሰብማለትምበጋራና በድርጅታዊ መንገድ ብቻ ለውጥ ይመጣል የሚለውን ሀሳብማናጋት ችያለሁ:: »ገፅ 422*

በመጨረሻምደራሲዋ *የሚከተለውን ታጫውተናለች::!..... ለሰው ልጅ ህይወት አክብሮት አንዲኖረን ለማድረግ:: መቻቻልና በሰላማዊ መንገድ አለመግባባትን መፍታትን በህይወቴ አንደጀግና ከምቆጥረው ከጌታቸው ማሩ የተማርኩትና* ሁሌም የበለጠ ለመስራት የምፈልገው ብርቱ *ጉዳይ ነው::»ገፅ 437*

*መፅሀፉ የተፃፈው*በእንግሊዘኛ *ነው:: ወደ አማርኛና ሌሎች የሀገራችን* ቋንቋዎች *ቢተረጎም* በተጨማሪም *ፊልም ሆኖ ወጣቱ ትውልድ ቢመለከተው ከዚህ ታሪካችን* ብዙ *ተምረን መልካሙን ይዘን* እንድንቀጥልስህተቱን *እንድናርምና*
*ወደፊት*እንድንራ*መድ*ይጠቅ*መናል::ደራሲዋ ሀላፊነቷን* በሚገባ *ተወጥታለች::ለጌታቸውም ያላትን* ጥልቅፍቅርና *አክብሮት አሳይታናለች::የውጭ* ቋንቋዎች *ተማሪ* በመሆ{ና ብዙ የእንግሊዘኛ *መፅሀፎች* በማንበብ፣በእንግሊዘኛ *መፃፍ ቢቀናትም*ለሰፊው *የሀገራችን* አንባቢ *ወደ ሀገራችን* ቋንቋዎች *ቢመለስ የሚጠቅመን ይመስለኛል::*

**Tower in the sky** (*የሰማይ ላይ ግንብ*) *ወደፊት*ከድህነት *ስንወጣ ለስንት ሰዎች ሀውልትማቆም አንዳለብን አሳይቶናል::የመፅሀፉ ደራሲም ሀውልት ከሚያስፈልጋቸው መከከል* አንዷ *አንደሆነች ከመፅሀፉ የበለጠ ማስረጃ አያሻም::ማጋነንምአይመስለኝም::* አኔ ጨርሻለሁ*ያላነበባችሁመፅሀፉን* በማንበብ *አንድጠቃሚ ነገር አንደምታገኙ አትጠራጠሩ::*

ቋቄቁሸቄቋቄቁሴሸቂሮሽቁ.ሰቄቂ